በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ወርሃዊ የአየር ጠባይ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከፌብርዋሪ 1-29/2024 የነበረው የአየር ጠባይ

## ግምገማ እንዲሁም

## ከማርች 1-31/2024

## የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ማርች 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 29/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ....- 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 29/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....- 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋርጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....- 3 -

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ....- 4 -

እ.ኤ.አ ከፌብሩዋሪ 1 እስከ 29/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ...- 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብሩዋሪ 1 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 5 -

እ.ኤ.አ ከፌብሩዋሪ 1 እስከ 29/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..- 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብሩዋሪ 1 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 5 -

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ ....- 6 -

ካርታ 6፡ እ.ኤ.አ ከማርች1-31, 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን ....- 6 -

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 7 -

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉ.ሀዉ. ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 7 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 29/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በፌብርዋሪ የመጀመሪያው እና የሁለተኛው አስር ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በሰሜን እና በሰሜን ምስራቅ እንዲሁም በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ጠንካራ የደመና ክምችት የተስተዋለበት ነበር፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ፣በመካከለኛው፣ በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በስርጭትም ሆነ በመጠን የተሻለ የዝናብ ሁኔታ የታየበት ወር ነበር፡፡

በአጠቃላይ በፌብርዋሪ ወር በደቡብና በደቡብ ምዕራብ፣በመካከለኛው፣በሰሜን እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከመካከለኛ እስከ ከባድ ማጠን ያለዉ ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል **በአዲስ አበባ ቦሌ** 14፣ 3.4፣ 3.1፣ 8.2፣ 13.1፣ 8.6፣ 56.2 **በአዲስ አበባ** 32.5፣ 3.3፣ 14፣ 9.2፣ 5.6፣ 2፣ **በሃዋሳ** 5.0፣ 6 **በኮምቦልቻ** 10.6፣ 6.2፣ **በደብረ ማርቆስ** 3.2፣ 24.4፣ **በቢሾፍቱ** 30፣ 6.2፣ 8፣10.6፣ **በጎሬ** 3.5፣ 17.8፣ 16.5፣ 9.4፣ 6.2፣ **በጅማ** 37.1፣ 3.5፣ 22.5፣ 6.9፣ 6.4፣ 5.6፣ **ሮቤ** 9.8፣ 30.4፣ 12.6፣ **በአይራ** 13.2፣ 5.5 **አለም ተፈሪ** 15.6፣ 3.6፣ 2.6፣ **በአማን** 5.1፣ 8.5፣ 10፣ 8.3፣ 10.9፣ 6.1፣1 1.2፣ 26.8 **እና** 11.2፣ **አንገር ጉትን** 10፣ 6.8፣ 8.6፣ **በአርጆ** 8.4. 18.6፣ 22.8 22.8 8.6 18.4 **በበደሌ** 6.4፣ 7.9፣ 29.7፣ 11.2፣ 6.6፣ 3.4፣ **በብላቴ** 22.2፣ 13.6. 5.2፣ 24.2 **በቦሬ** 2.9፣ 8.5፣ 5፣ 6.3፣ 10.4፣ **በጨፋ** 16.5፣ 3.5፣ 5.6፣ 5.6 **በደብረ ብርሃን** 5.4፣ 4.5፣ 19.8፣ 12.8፣ 3.6፣ **በደምቢ ዶሎ** 6.8፣ 5.2፣ 9.5፣ 5.2፣ **በኢጃጂ** 11.7፣ 14.4፣ 14.2፣ 12.2፣ 3.8፣ 16.2፣ 4.5፣ **በግዮን** 31.4፣ 14.6፣ 10፣ **በፍቼ** 16.1፣ 7፣ 11.7፣ 5.3፣ **በጋቲራ** 26.7፣ 21፣ 28.4፣ 25.6፣ 35.8፣ 15.6፣ 38.6፣ 15.7፣ 7.6፣ 13.6፣ 20.4፣ 29.6፣ **በሆሳና** 3.8፣ 4.1፣ 25.6፣ 3.4፣ 4.9 15.3፣ 8.8፣ **በካቺሴ** 5.4፣ 10.7 16.8፣ 5.8 **በቁለምሳ** 29.8. 49.7፣ 14፣ 26.8 ፣ **በሊሙገነት** 40፣ 10፣ 10፣ 6.1፣ 7.9፣ 4.9፣ 9፣ **በጂንካ** 3.6፣ 17.2፣ 7፣8.2፣ 10.2፣ 7.5፣ 3.4፣ 22.9፣ 25.4፣ 5.1 ፧ **በማጂ** 70.5፣ 8.7፣ 8.5፣ 15፣ 50፣1 0.5፣ 5.7፣1 3.2.11፣ **በመካነሰላም** 15.2፣ **በማሻ** 57.5፣ 30.2፣ 12.0፣ **በሳውላ** 4.2፣ 17.6፣ 4.6፣ 6.2፣ 18.8፣ 6.5፣ 5.2፣ 10.2፣ 30.8፣ **በስሪንቃ** 49.4፣ **በአቦምሳ** 8.8፣ 19.5፣ 20፣ 36.6 **በሻምቡ** 14.7፣ 2.6፣ 13.9፣ 9.5፣ **በቴፒ** 4.7፣ 3.9፣ 22.3፣ 35፣ 7.5፣ 10.3፣4 .9፣ **በተርጫ** 12.5፣ **በወላይታ ሶዶ** 2.3 **በወራቤ** 3.9፣ 5.9፣ 11.4፣ 10.7፣ 13.4 **እንዲሁም በባቱ** 16.3፣ 5፣ 5.6 **በሚ.ሜ** ይገኙበታል።




ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት በፌብርዋሪ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ፤የሲዳማ ክልል እና የምዕራብ ኦሮሚያ ክልል ዞኖች፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባ ላይ ከ31-300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-16 ቀናት ያህል የነበራቸው ሲሆን፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ቦረና፤ ከአማራ ክልል ደቡብ ጎንደር፣ አዊ ዞን፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፣ ሰሜን ሸዋ፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ካማሺ ዞን፤ ሁሉም የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ዞን 2፤4፣1 እና 5፤ ከሱማሌ ክልል ዳዋ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች ከ6-30 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-4 ቀናት ያህል ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2) ፡፡


ባለፉት በፌብርዋሪ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከጋምቤላ ክልል የማዣንግ ዞን፤ ከአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን፣የደቡብ እና የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ደቡብ ጎንደር፣ ዋህግምራ፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ጂማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፤ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አርሲ፣ ምስራቅ ጉጂ እና ቦረና፤የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፤ ጋምቤላና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ35-42.5 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1) ።




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 29/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፤ ጋምቤላና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ35-42.5 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1 ) ።





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## እ.ኤ.አ ከፌብሩዋሪ 1 እስከ 29/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈው ወር በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይና እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች በተለይም በመጀመሪያውና በሁለተኛው አስር ቀናት ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው የእርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አመላካቾች ያሳያሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን በማሻሻል የበልግ ወቅት የማሳ ዝግጅትን አስቀድሞ ለመጀመርና ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራት፤ የግብርና ግብዓቶችን አስቀድሞ ለማቅረብና ለማሟላት እንዲሁም ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት ማሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም የነበረው ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር እንዲሁም የአረንጓዴ ዕጽዋት ልምላሜና ሽፋንን ከማሻሻል አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4)፡፡




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብሩዋሪ 1 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት

## እ.ኤ.አ ከፌብሩዋሪ 1 እስከ 29/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ወር በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛው እና በመካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ በመካከለኛውና በታችኛው አባይ፣ በጥቂት የታችኛው ገናሌ ዳዋ፣ በላይኛው አዋሽ፣ በስምጥ ሸለቆ ኪስ ቦታዎች እንዲሁም በላይኛው አዋሽ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ነበራው (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብሩዋሪ 1 እስከ 29/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በማርች ወር የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መደበኛ ቦታዎቻቸውን እየያዙና እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ጊዜ ሲሆን፣ በተለይም በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከሚፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ ይኖራል፡፡

በሚቀጥለው የማርች ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተጠናከሩ ይመጣሉ፡፡ ስለሆነም በተለይም ከወሩ አጋማሽ ጀምሮ ቀስ በቀስ ወደ ደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ ቦታዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ይበልጥ እየተስፋፋና እየተጠናከረ እንደሚመጣ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6፡ እ.ኤ.አ ከማርች1-31, 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በማርች ወር በአብዛኛዎቹ የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ ክፍሎች በመጠንም ሆነ በስርጭት ከእለት ወደ እለት የተስፋፋና የተጠናከረ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን በማሻሻል አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ሰብሎች የእድገትና የብቅለት ሁኔታ ምቹ ከማድረግ አንጻር፣ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት ለመሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሟላት አንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የበልግ አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች አስፈላጊውን ግብዓት በማሟላት የግብርና ስራዎችን ለማከናወን ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በማርች ወር በአብዛኛዎቹ የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት ተፋሰሶች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት የተሻለ እርጥበት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ አዋሽ፣ ስምጥሸለቆ፣ ገናሌዳዋ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ባሮአኮቦ፣ ዋቢሸበሌ፣ አባይ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ያገኛሉ፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et